ፍኖተ

# ነፃነት

ፍኖተ ነፃነት የካቲት 30 ቀን 2005 ዓ.ም. ቁጥር 67

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

## “በኃይማኖት ነፃነት ጥያቄ የታሰሩ ዜጎችም የህሊና እስረኞች ናቸው”

### አቶ ዳንኤል ተፈራ
### የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ



## የፓርቲዎቹ መሰባሰብ ለነፃነት ትግሉ ምን ይፈይድ ይሆን?

6

## ሰልጣኞቹ የምርጫ ቦርድ ስልጠና ገንዘብ ከማባከን ያለፈ ጥቅም የለውም አሉ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በየጊዜው የሚያዘጋጀው ስልጠና ስብሰባ ምንም ፋይዳ የሌለው ነው ሲሉ አንዳንድ ከተለያየ ክልል የተውጣጡ ሰልጣኞች ለፍኖተ ነፃነት ገለፁ፡፡

አስተያየት ሰጪዎቹ “ምርጫ ቦርድ ስልጠና ስብሰባ እያለ በየጊዜው በሚዲያ የሚያስነግረው ማስታወቂያ ለእርዳታ ልመና እንጂ ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ፋይዳ የለውም” ብለዋል፡፡ እነዚህ አስተያየት ሰጪዎች እንደሚሉት “ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ የተዘጋጁ ማንዋሎችና የአፈፃፀም መመሪያዎች ተመሳሳይ ናቸው፡፡ የአካባቢ ምርጫ አስፈፃሚዎች የሚመለመሉት በየአካባቢው ካድሬዎችና ደህንነቶች ነው፡፡ መስፈርቱ ለኢህአዴግ ታማኝና ታዛዥ መሆን ነው፡፡ ምርጫ አድርገው ሲያጠናቅቁ ውለታ መጠየቅ ነው፡፡” ይላሉ አያይዘውም “ምርጫ ቦርድ በየምርጫ ወቅት በየስብሰባው ጊዜ ጠርቶ የሚሰጠው ትምህርትም ስልጠናም ተመሳሳይ ነው፡፡ አዲስ ነገር የለውም በየጊዜው የሚሰበሰበውና አስር ጊዜ ማስታወቂያ የሚያስነግረው በዲሞክራሲ ስም የሚያገኘውን ገንዘብ ለማወራረድና ምርጫ ቦርድ ስራ እየሰራ ነው ለመባል ነው፡፡” በማለት ተችተዋል፡፡

ለፍኖተ ነፃነት ስማቸው እንዳይጠቀስ የጠየቁት አስተያየት ሰጪዎቹ እንደሚናገሩት በየደረጃው ያሉ የምርጫ ቦርድ አመራርና አስፈፃሚዎች በፖለቲካ እምነታቸው የኢህአዴግ አባላትና አፍቃሪ ኢህአዴግ ናቸው፡፡ ከዝቅተኛ የመንግስት ሰራተኛነት የተገኙ ስለሆኑ በራስ የመተማመን መንፈስ አለመኖር፣ በህግ የተሰጣቸውን ስልጣን ተግባራዊ እናደርግ ቢሉም የአቅም ችግር አለባቸው፡፡ “አሁን ምርጫ ቦርድ እየሰራ ያለው ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ አለ ብሎ ስለሚያምን ሳይሆን በዚህ ዓይነት ‹ምርጫ›፣‹ምርጫ› እየተባለ አዲስ ትውልድ እስከፈጠር ድረስ መቆት ነው” በማለት አስተያየታቸውን ደምድመዋል፡፡

በዚህ ዙሪያ የምርጫ ቦርድ የስራ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ያደረግነው ጥረት ለጊዜው አልተሳካም፡፡

## ምርጫ ቦርድ ሆይ!

2

## ኢትዮጵያ ለአቅመ ምርጫ አልደረሰችም

## ርእሰ አንቀጽ

# ምርጫ ቦርድ ሆይ!

## ኢትዮጵያ ለአቅመ ምርጫ አልደረሰችም

የደርግ መውደቅን ተከትሎ በሀገራችን የታየው የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ጅምር ህገ- መንግስታዊ ዋስትና ቢያገኝም፣ 21 ዓመት ሙሉ እውነተኛ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት አልሰፈነም፡፡ አምባገነን ገዥዎቻችን መድብለ ፓርቲ በሀገሪቱ መኖሩን ለማስረዳት የምርጫ ቦርድን መቋቋምና በርካታ ፓርቲዎች መኖራቸውን በተደጋጋሚ ቢገልፁም፣ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ሊኖር የሚችለው ብቁ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት፣ ሀቀኛ የምርጫ አስፈፃሚ ተቋምና በፓርቲዎች መካከል ተመጣኝ ፉክክር ሲኖር ብቻ ነው፡፡

በሀገራችን እንደሚታየው ግን ገለልተኛ የምርጫ አስፈፃሚ ተቋም የለም፡፡ ባለፉት አመታት ገዥው ፓርቲ በማን አለብኝነት የመንግስትንና የፓርቲን መስመር ተላልፎ የመንግስትን ገንዘብ እንዳሻው እየተጠቀመ፣ በህግ ባልተፈቀደ የንግድ ስራ ውስጥም ጭምር በመሳተፍ ገንዘብ እያጋበሰ በሌላ በኩል የፅ/ቤት ክፍያቸውን ለመክፈል ካቃታቸው ተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ለዛውም ነፃ አወዳዳሪ በሌለበት "ሲወዳደሩ" ተመልክተናል፡፡ ቦርዱ በተለያዩ ወቅቶች ለፓርቲዎች የሚያከፋፍለው የገንዘብ ድጋፍ ቀመርም አድሏዊና ኢህአዴግን ይበልጥ የሚጠቅም ነው፡፡ ምርጫ ቦርድ በየጊዜው ለሚደረጉ ሀሳዊ ምርጫዎች የሚያባክነው ገንዘብ ለዴሞክራሲ ግንባታ ቢውል ሀገሪቱን በዴሞክራሲ ጎዳና አንድ እርምጃ ያራምዳት ነበር፡፡ ህዝቦቿን ለመመገብ የውጪ ረድኤት የምትማፀን ሀገር አሸናፊው ሁልጊዜ ቀድሞ ለሚታወቅበት ሀሳዊ ምርጫ ገንዘብ ማባከን የለባትም ብለን እናምናለን፡፡

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ኢህአዴግ ብቻውን ‹‹ለሚወዳደርበት›› የሚያዚያው የአካባቢና የከተማ መስተዳድር ምርጫም ከፍተኛ ገንዘብ መድቧል፡፡ ይህ ገንዘብ የኢትዮጵያን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ባለመዋሉ በከንቱ እንደባከነ ለመገንዘብ አይከብድም፡፡ ቦርዱ በተለያየ ጊዜ የሚያካሄዷቸው ስልጠናዎችም በየክልሉ ያሉ የምርጫ አስፈፃሚዎችን አቅም ከመገንባት ይልቅ የተለመዱ/ ተደጋጋሚ አጀንዳዎችን የሚነሱባቸው መሆናቸውን ተሳታፊዎች ይናገራሉ፡፡ ታዲያ በስልጠና ሰበብ በታላላቅ ሆቴሎች የሚበተነው ገንዘብ በከንቱ አልባከነም የሚል ይገኝ ይሆን?

ለስልጠናና በምርጫ ሰበብ የሚባክነውን ገንዘብ የተፎካካሪ ፓርቲዎችን አቅም ለመገንባት እንዲያገለግል ሊደረግ ይገባዋል፡፡ ተመጣጣኝ አቅም በሌላቸውና በምርጫ አስፈፃሚ አካል እኩል በማይታዩ ፓርቲዎች መካከል ምርጫ የማይታሰብ ነው፡፡ በመሆኑም መንግስትና ምርጫ ቦርድ በኢትዮጵያ እውነተኛ ምርጫ ይደረግ ዘንድ ቁጠኝነት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ፓርቲዎቹ ተመጣጣኝ የፉክክር አቅም ሊፈጥሩ ያልቻሉት በራሳቸው ድክመት ባቻ ሳይሆን በአመዛኙ በገዢው ፓርቲ በሚደርስባቸው ኩርኮማ መሆኑ የአደባባይ ሀቅ ነው፡፡

ምርጫ ቦርድ ኢህአዴግ መጠቀሚያነቱን በመተው ኢትዮጵያችን ለአቅመ ምርጫ እንድትደርስ ኃላፊነቱን ይወጣ እንላለን፡፡

# የዛሬ በጀርመን የአድዋ ድል ይዘከራል




በጀርመን የኢትዮጵያውያን ሲቪክ ማህበረሰብ የተባለ ተቋም በጀርመኗ ቩዝቡርግ ከተማ የአድዋ ድል በዓልን ለመዘከር ታወቀ፡፡በስፍራው ለፍኖተነፃነት ጋዜጣ ድጋፍ እንደሚደረግ ይጠበቃል፡፡

"ታሪካችን ጥንካሬያችን ነው" በሚል መሪ ቃል የሚከበረው የአድዋ 117ኛ የድል በዓል ላይ በዓሉን የሚመለከቱ ንግግሮች እና የተለያዩ የመዝናኛ ዝግጅቶች እንደሚቀርቡ ተቋሙ አስታውቋል፡፡ በበዓሉ ላይ ንግግር የሚያደርጉት ዶ/ር አሰፋ ነጋሽ ከሆላንድ እንዲሁም ጋዜጠኛ አዲስ ሙሉግታ ከጀርመን እንደሆኑ የተገለፀ ሲሆን ታሪካዊና ባህላዊ ትርኢቶችም በዝግጅቱ እንደሚካተቱበት ተጠቁሟል፡፡

በተያያዘ ዜና በጀርመኗ ቩዝቡርግ ከተማ በሚደረገው የአድዋ ድል በዓል መታሰቢያ ዝግጅት ላይ አንድነት ፓርቲ ለፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ የማሽን ግዢ ስለጀመረው የገቢ ማሰባሰቢያ በስፍራው የሚገኙት በአቶ መኮንን ታዬና የጋዜጣው ኤዲቶሪያል ቦርድ ተወካዮች ከአዲስ አበባ ማብራሪያ እንደሚሰጡ ታውቋል፡፡





# 33 ቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ተፈራረሙ



ጥቅምት 15 ቀን 2005 ዓ.ም ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በአዳማ ላይ በጠራው ስብሰባ ፒቲሽን የተፈራረሙበት 33ቱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከምርጫ ባሻገር በጋራ ሊያታግላቸው በሚችሉ 13 ነጥቦች ላይ የመግባቢ ሰነድ ተፈራረሙ፡፡

የካቲት 23 ቀን 2005 ዓ.ም በመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በተከናወነው የፊርማ ስነ-ስርዓት ላይ በትብብሩ በጋራ የሚከናወኑ ተግባራት 13 ነጥቦች ተዘርዝረዋል፡፡ በተዘረዘሩት 13 ነጥቦች ውስጥ መንግስት የሀገርንና የህዝብ ዘላቂ ጥቅሞችን በሚጎዱ እርምጃዎ ላይ ተወያይቶ የጋራ አቋም መያዝ፣ መግባቢያ ሰነዱን በፈረሙ ፓርቲዎች ወይም አባሎቸው ላይ መንግስት ወይም ገዥው ፓርቲ ህገ-ወጥ እርምጃ ሲወሰድ በጋራ በአንድነት መቆም፤ ምርጫን በተመለከተ የጋራ ስልት መቀየስ፤ የእቅዱ ማስፈፀሚያ የሚውል የፋይናንስና ማቴሪያል ድጋፍ በጋራ መሰብሰብ፤ በተቃዋሚዎች መካከል ጤናማ ግንኙነት እንዲፈጠር ማድረግ የሚሉ ነጥቦች ይገኛሉ፡፡ ፓርቲዎቹ ለዚህ ስምምነት የደረሱት ለአራት ተከታታይ ወራት እየተነገናኙ ውይይት ካደረጉ በኋላ መሆኑን በፊርማው ስነ-ስርዓት ላይ ተጠቅሷል፡፡

በፊርማ ስነ-ስርዓቱ ላይ የተለያዩ የፓርቲ ተወካዮች፣ዲፕሎማቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦችና የሚዲያ ባለሙያዎች ተገኝተው ሂደቱን ተከታትለዋል፡፡ ከፊርማ ስነ-ስርዓቱ በኋላ የትብብሩ ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴው ለጋዜጠኞች መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ አስተባባሪዎቹ በጋራ በመሆን በሰጡት መግለጫ ‹‹ትግሉን አንድ ደረጃ ከፍ ማድረግ አለብን፣ በርካታ ፓርቲዎች መሰብሰባችን ጥንካሬ ይፈጥርልናል፣ ህዝብ የፓርቲዎች ባለቤት መሆን አለበት፤ የተቃዋሚዎች ጥንካሬ በህዝብ ጥንካሬ ይወሰናል፤ እኛ 13ቱን ነጥቦች ለመተግበር ስንቀሳቀስ ህዝብ ጉዳዩ የእኔ ነው ብሎ በትግሉ ውስጥ ሊሳተፍበት ይገባል፡፡›› በማለት ተናግረዋል፡፡



# “በኃይማኖት ነፃነት ጥያቄ የታሰሩ ዜጎችም የህሊና እስረኞች ናቸው”

## አቶ ዳንኤል ተፈራ
## የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ



**የአንድነት ፓርቲ በአሁን ወቅት ምን አይነት እንቅስቃሴ እያደረገ ነው? እርስዎ የሚመሩት የህዝብ ግንኙነት ስራስ እንዴት ነው?**

ፓርቲያችን ባቀደው የ5 ዓመት ስትራቴጂ መሰረት 33 ፓርቲዎችን በማሰባሰብ እንደ አንድ ፓርቲ የሚጠበቅበትን ከሌሎች ጋር በመሆን ትልቅ ስራ ሰርቷል፤ እየሰራም ይገኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድነት አንዱ የመድረክ አባል እንደመሆኑ መጠን ለመድረክ ተጠናክሮ እዚህ መድረስ የሚጠበቅበትን የራሱን ድርሻ እየተወጣ ይገኛል፡፡ ሌላው በህዝቡ ውስጥ የራሱን የፖለቲካ ስራ በመስራት በፊት ከነበሩን አባላት በበለጠ በርካታ ታታሪ ወጣት ምሁራንን ጨምሮ ሌሎች ጠንካራ አባላትን በመመልመልና ለትግል በማብቃት ወደ አመራር ስልጣን በማምጣት የሀገራቸው ጉዳይ ላይ ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ በማድረግ ጥሩ ስራ ሰርቷል፤ እየሰራም ይገኛል፡፡

የህዝብ ግንኙነት ስራን በተመለከተ ኢህአዴግ ባጠበበው የፖለቲካ ምህዳርም ቢሆን የፓርቲውን እንቅስቃሴ ለህዝብ በማድረስ፤ የህዝቡን ፍላጎት፣እንቅስቃሴና ነባራዊ ሁኔታ በመከታተል ለፓርቲው ያቀርባል፤ የመፍትሄው አካልም በመሆን ከሌሎች አመራሮች ጋር በጋራ ይሰራል፡፡ በህዝቡ ላይ የሚፈጠረውንም በደል ከበቂ መረጃና ምክንያት ጋር በመቃወም ጋዜጣዊ መግለጫ መስጠት እያጋለጠ፣ የሚፈፀሙ በደሎችም እንዲቆሙና የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ በመታገል ላይ ይገኛል፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በነፃነት እንዲወያዩና የመፍትሄውም አካል እንዲሆኑ አዳራሽ ተከራይተን ህዝቡን ለማወያየት ብንከለከልም በየሳምንቱ መድረክ አዘጋጅተን ህዝቡ ከፍርሃት እንዲወጣና ለመብቱና ለነፃነቱ እንዲታገል አዲስ አበባ ባለው ዋና ፅ/ቤት ዜጎች እንዲወያዩ እያደረግን እንገኛለን፡፡ ይሄንን ውይይት በተለያዩ ክልሎችም ተግባራዊ ለማድረግ እየተንቀሳቀስን እንገኛለን፡፡

**በሀገሪቱ ያለውን አፈናእና እስር እንዴት ይገልፁታል?**

ለመግለፅ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም ዜጎች የመብት ጥያቄ በማንሳታቸው ብቻ እንደወንጀለኛ አሸባሪ ተብለው ይፈረጃሉ፡፡ ለምሳሌ ፖለቲካ አመራሮችና ሙስሊም ወንድሞቻችን የኃይማኖት ነፃነት ጥያቄ በማንሳታቸው እራሱ መንግስት ከሶ ውሳኔ ሳይሰጥ እራሱ ከፍ/ቤት ቀድሞ በኢቴቪና በሬዲዮ አሸባሪ ይላል፡፡ ጋዜጠኞችም በሀገሪቱ ያለውን እውነታ በመፃፋቸው ብቻ አሸባሪ ተብለው ወህኒ ቤት ይወርዳሉ፣ ሌሎች ደግሞ እንዳይሰሩና እንዳያሳትሙ ይከለከላሉ፤ ቀሪዎቹ ሀገር ጥለው እንዲሰደዱ ተደርጓል፤አሁንም እየተደረገ ነው፡፡

በተለይ አንድነት በፖለቲካዊና በኃይማኖት የነፃነት ጥያቄ መብቶቻቸውን በመጠየቃቸው የታሰሩ ወገኖቻችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ እየታገልን ነው፡፡ በሀገራችን ካለፈው 50 ዓመት ጀምሮ ዜጎች ሓሳባቸውንና መብቶቻቸውን በመጠየቃቸው ብቻ ዛሬም ድረስ እየታሰሩ ይገኛሉ፤ ይህ ሳንጄና ለመጨረሻ ጊዜ በሀገራችን እንዲያበቃ፣ ለዚህም ፓርቲያችን የታሰሩት የፖለቲካና የህሊና እስረኞችን በማሰብ ሁሌ ወር በገባ በ 3ኛው ቀን ከሰዓት በኋላ የሻማ(የጧፍ) መብራት እናካሂዳለን፡፡ አንድነት በኃይማኖት ነፃነት ጥያቄ የታሰሩ ዜጎችም የህሊና እስረኞች ናቸው ብሎ ያምናል፡፡

**ወቅታዊውን የሀገራችን የፖለቲካ ችግር ለመፍታት ምን እየደረጋችሁ ነው?**

በሀገሪቱ ላይ ያለው የመልካም አስተዳደር እጦት፣ የኑሮ ውድነት፣ ሙስና መባባስና የመንግስት አምባገነንነት ከበፊቱ በበለጠ ሁኔታ ተጠናክሮ በመቀጠሉ የሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ ይሄ ደግሞ አንድነትንም ሆነ መድረክን እጅግ ስለሚያሳስበው መንግስትንም ሆነ ኢህአዴግን የሀገሪቱ ጉዳይ ከድጡ ወደማጡ እየሄደ ስለሆነ በግልፅ እንወያይና በጋራ በፍትሄ እናብጅለት ብለን በተደጋጋሚ በደብዳቤ ብንጠይቅም እስካሁን ምላሽ አላገኘንም፡፡ ስለዚህ አንድነት አቅም በፈቀደ መልኩ ይህን ችግር የፈጠረውን አምባገነን ስርዓት ሳንጄና ለመጨረሻ ጊዜ ለማስወገድ በሚከተለው ሰላማዊና ህጋዊ የፖለቲካ ትግልና በነደፈው ስትራቴጂ መሰረት የራሱን ስራ እየሰራ ይገኛል፤ ጥሩ ውጤት እንደሚመጣም እናምናለን፡፡

**ከአንድ ወር በፊት የራሳችሁን ማተሚያ ማሽን በመግዛት ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣን ወደ ህትመት ለመመለስ ዘመቻ ጀምራችኋል ከህዝቡ ቀና ግብረ መልስ እያገኛችሁ ነው?**

አዎ፤ ጥሩ ግብረ መልስ እያገኘን ነው፡፡ የፓርቲያችን ልሳን ከመሆን በተጨማሪ የህዝቡ አማራጭ የመረጃ ምንጭ በመሆን ስታገለግል የነበረችውን ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣችንን መንግስት በህገወጥ መንገድ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅትን ጨምሮ በሌሎቹም ማተሚያ ቤቶች እንዳናሳትም በመደረጉ ህትመቱ መቋረጡ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ፓርቲው በ 4 ወራት ጊዜ ውስጥ የተቋረጠውን የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ጨምሮ ለተለያዩ የፓርቲው ህትመት





# ያላዋቂ ሰሚ ያላዋቂ ፀሀፊ ሁለቱም ለቅላቂ አንዱ ቀለም አንዱ …

ከቀለሙ ሁነኛው

“ያላዋቂ ሳሚ …ይለቀልቃል” ይላሉ አበው፡፡ እርግጥ ነው መሳሳም በራሱ ጥበብ ነው፡፡ የጥበብ እሳት ማቀጣጠያ ጥበብ፡፡ ያላዋቂ ፀሀፊም ቀለም ለቅላቂ ነው፡፡ በተለይ ጋዜጠኛ ተብዬ ሲሆን፡፡ ለዚህ ፅሁፍ መነሻዬ የካቲት 27/ 2005 የጋዜጣ ርዕስ አንቀፅ ይዞ የወጣው ፅሁፍ ነው፡፡ “የፖለቲካ ትብብር ማለት ፓርቲዎችን እንደ መንደር ማሰባሰብ አይደለም” በሚል ርዕስ የወጣው ፅሁፍ እጅግ ከማሳዘኑም በላይ የአዘጋጆቹን ማንነት ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ እውን እንደ ሰንደቅ ጋዜጣ አዘጋጆች አገላለፅ የመድበለ ፓርቲ ስርዓት ግንባታ በአገራችን ዋስትና አግኝቷል? ገዥው ፓርቲ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ፅ/ቤት እንዲኖራቸው በስብሰባዎች ወደ ህዝቡ እንዳይደርሱ በገንዘባቸው እንኳን የሆቴል አዳራሾችን እንኳ እንዳይከራዩ እያዘዘ፣ አንድነት ፓርቲ “ፍኖተ ነፃነት” እያለ የሚያሳትመውን ጋዜጣ ከህትመት ውጪ እንድትሆን እያደረገ እያየን የሰንደቅ ጋዜጣ አዘጋጆች “ለምን በሬ ወለደ” ይላሉ? ጋዜጠኛ እውነትን አብሳሪ ሀቅን ዘካሪ እንጂ ቀጣፊ ብዕር ሊኖረው አይገባም፡፡ በአገሪቱ ለ76 ፓርቲዎች መፈጠር ግንባር ቀደም ተጠያቂ ኢህአዴግ እንጂ ተቃዋሚዎች አይደሉም፡፡ እንደ 97ቱ ቅንጅትና ህብረት የመሳሰሉ ጠንካራ የፓርቲዎች ስብስብ ሲፈጠር ኢህአዴግ ግንባር ቀደም አመራሮቹን “አሸባሪ” በሚል ተራና ተልካሻ ምክንያት ቃሊቲ እንደወረወራቸው ለሰንደቅ ጋዜጣ አዘጋጆች ማን በነገራቸው! ኢህአዴግ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ስብስብ እንደማይፈልግ እንኳን ፊደል የቆጠረ በጣቱ የሚፈርም ኢትዮጵያዊ ያውቃል፡፡ እንኳንስ የሰንደቅ ጋዜጣ አዘጋጆች፡፡ የርዕሰ አንቀጹ ፅሁፍ ስህተቱን የሚጀምረው ከርዕሱ ነው፡፡ አዘጋጆቹ ስላልገባቸው እንጂ በመንደር የሚሰባሰብ አርሶ አደር ማህበራዊ መስተጋብሩ እጅግ የጠነከረ ይሆናል፡፡ ከተበታተነ ግንኙነት ይልቅ በቅርበት ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በየጊዜው ለመገማገምና ልምድ ለመለዋወጥ በመንደር መሰባሰቡ ውጤታማ ያደርገዋል፡፡ የገጠሩን አርሶ አደር ደርግ በመንደር ማሰባሰብ ጀመረ፤ ኢህአዴግም አዋጭነቱን አጢኖ ቀጠለበት፡፡ አሰይ! ተቃዋሚ ፓርቲዎችም በመንደር ይሰባሰቡ! ጉርብትናቸው ሲጠናከር ቤተሰብ ይሆናሉ፡፡ የዚያን ጊዜ የሰንደቅ ጋዜጣ አዘጋጆችም ብዕራቸው እውነትን ትዘክር ይሆናል፡፡

ቸር እንሰንብት!

# ኦፌኮ ህጋዊ እውቅና አገኘ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት (መድረክ) አባል ድርጅቶች የሆኑት የኦሮሞ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን) እና የኦሮሞ ህዝብ ኮንግረስ (ኦህኮ) ውህድ የሆነው ኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ (ኦፌኮ) ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ህጋዊ ሰርተፊኬት ማግኘቱን ከፓርቲው ጽቤ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

የውህዱ ፓርቲ ዋና ጸሐፊ ሆኑት አቶ በቀለ ነጋ በተለይ ለፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ እንደተናገሩት “አንድነት ኃይል ነው፡፡ ሁለቱ ፓርቲዎች በመዋሀዳቸው ለኢህአዴግ ሥጋት ለትግሉ ደግሞ ጥንካሬን ይፈጥራል፡፡ አንድ መሆናችን በፋናንስም ፣ በሰው ኃይልም ጉልበት እንፈጥራለን፡፡ ይህ የወቅቱ ጥያቄ ነው፡፡ የኦሮሞ ህዝብ አንድ ሆነን እንድንቀርብ በተደጋጋሚ ጠይቆናል፡፡ ህዝባችንን ጥያቄ መልሰናል፡፡ ከእንግዲህ ህዝብ ከጎናችን እንዲቆም እንጠይቃለን፡፡ ይህ የኦፌዴንና የኦህኮ አርኣያነት ሌሎች ፓርቲዎችም ሊከተሉት ይገባል፡፡ ዳርና ዳር ቆሞ ድንጋይ መወራወሩ ትግሉን ጎድቷል፡፡ ልዩነትን አክብሮና አጥብቦ ተቻችሎ በመዋህድ ትግሉን እንዲጠናከሩ መልእክቴን ማስተላለፍ እፈልጋለሁ” ብለዋል፡፡ የውህዱ ፓርቲ ፕሬዝዳንት አቶ ገብሩ ገ/ማሪያም “ተቃዋሚዎች 70 እና 80 ቦታ ተሰነጣጥቀን በመቆታችን ኢህአዴግ ላይ ተፅዕኖ መፍጠር አልቻልንም፡፡ ውጤትም አላመጣንም፡፡ የኦህኮና የኦፌዴን ውህደት የኦሮሞ ህዝብን ጥያቄ ነው፡፡ የተቃውሞውን ጎራ አንድ እርምጃ ወደ ፊት የሚያራምድ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ለዴሞክራሲዊ ሥርኣት ግንባታና ለአገር ብልፅግናም አስተዋጽኦ አለው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብም በተቃዋሚዎች ጎን ተሰልፎ ታሪካዊ የዜግነት ኃላፊነቱን እንድወጣ ጥሪዬ አቀርባለሁ” ብለዋል፡፡

ስራዎች የሚያገለግል የማተሚያ ማሽን ለመግዛት በይፋ በምናደርገው እንቅስቃሴ ህዝቡ በገንዘብ፣ በሐሳብና በሞራል በሀገር ውስጥና በውጭ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ከፍተኛ ድጋፍ እየሰጡን ይገኛሉ፡፡ ይሄ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ ለማሽን መግዣ የገቢ ማሰባሰቢያው በተለያ መልኩ አስተዋፅዖ ላደረጉትና እያደረጉ ላሉ ሁሉ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡ ስለዚህ ከህዝቡ ጥሩ ድጋፍ አግኝተናል፤ እያገኘንም ነው፡፡

**አምባገነን ፓርቲን አጅበን አንወዳደርም በማለት ከምርጫ ወጥታችኋል፤ ከዚህ ያለፈ ምን እርምጃ ወስዳችኋል?**

በቂ ነው ባይባልም የተወሰኑ እርምጃዎችን ወስደናል፤ በዚህም ኢህአዴግ አጣብቂኝ ውስጥ እንዲገባ አድርገናል፡፡ እዚህ ላይ ካሁን ቀደም በኢህአዴግ፣ በመንግስትና በምርጫ ቦርድ መካከል ምንም ልዩነት ሳይኖር አንድ መሆናቸውንና ሁሉም በኢህአዴግ መዳፍና መዘውር በመሆናቸው እያወቅን ምርጫ ላይ እንሳተፍ ነበር፤ ያ ደግሞ አምባገነን ስርዓትን ማበረታታትና ማጀብ ስለሆነ ለሀገሪቷም ሆነ ለህዝቡ እንዲሁም ለፓርቲያችን ምንም ጥቅም ስላልሰጠ ከሌሎች ለሀገርና ለወገን ከሚያስቡ ፓርቲዎች ጋር በመሆን ለተጠየቁት ጥያቄዎች ምላሽና ማስተካከያ እርምት እስካልተሰጠ ወደ አጃቢነት ምርጫ እንደማንገባ ግልፅ አድርገናል፡፡ በዚህም መሰረት ጥያቄችን ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ ከመንግስትና ከኢህአዴግ ምንም ምላሽ ባለመገኘቱ 33ቱ ፓርቲዎች ሚያዚያ 2005 ዓ.ም. በሚደረገው የአዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ አስተዳደርና የአካባቢ የይምሰል ምርጫ ላይ እንደማንሳተፍ በተግባር በማሳየት ኢህአዴግ ሲያታልላቸው ለነበሩት ለጋሾችና ለሀገራችን ህዝብ እውነታውን በማጋለጥ የክስረት ውጥረት ውስጥ እንዲገባ አድርገናል፡፡

በአሁን ወቅት በተለያዩ የምርጫ ጣቢያዎች ተወዳዳሪው ኢህአዴግ ብቻ መሆኑን በተግባር ማረጋገጥ ትችላለህ፤ ይህ ደግሞ ኢህአዴግ ከደርግ ባልተለየና ምናልባትም በባሰ መልኩ ምን ያህል አምባገነን እንደሆነ ከድርጊቱ እንዲታይ በማድረግ የራሳችንን ፖለቲካዊ እርምጃ ወስደናል፡፡

ወደ ፊት ደግሞ በምንከተለው የሰላማዊ ትግል ስልት የተለያዩ እርምጃዎችን ስለምንወስድ ያኔ እናየዋለን፤ እኛ ግን በዚህ አናበቃም፡፡ ምክንያቱም በሀገሪቱ የኃይማኖት ነፃነት እጦትን ጨምሮ በርካታ ችግሮች እጅግ እየተባባሱ መምጣታቸውን በዝምታ የምናልፍበት ጊዜ ላይ አይደለንም፡፡

ሁሌም ቢሆን አምባገነኖች የሚሸነፉት በህዝብ ነውና፤ ጠንካራ የህዝብ ድጋፍ ካለ ያሰብከውን የማታሳካበት ምክንያት የለም፡፡ የአንድነት ፓርቲ ዋነኛ ዓላማም ሀገራችን ኢትዮጵያ የሁላችንም እንደመሆኗ መጠን ሁሉም ዜጎች በምቾት፣ ያለ አድሎ በእኩልነት ሀብቷን በመጠቀም ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተከበሩባት ሀገር እንድትሆን ነው፡፡

**እናመሰግናለን**

# የፓርቲዎቹ መሰባሰብ ለነፃነት ትግሉ ምን ይፈይድ ይሆን?

በዴሞክራሲያዊ መንገድ በሚደረግ ምርጫ ስልጣን እንይዛለን በሚል እምነት ከ70 የሚበልጡ ፓርቲዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ የፓርቲዎቹ ቁጥር መብዛት ለሀገራችን የነፃነት ጉዞ የሚፈቅደው ባይኖርም፣ የቁጥር መብዛቱ በራሱ የስርዓቱን አምባገነንነት የሚያሳይ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ፓርቲዎች ስርዓቱ በሚከለተው ዘርን መሰረት ያደረገ ፖለቲካ የሚወክሉት ብሔር መጨቆኑን በመግለፅ በየአካባቢው የተቋቋሙ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ሰላማዊ ትግሉን ለማቀጨጭና የኢህአዴግ አምባገነናዊ ስርዓት እንዲቀጥል እንዲረዱ በስርዓቱ ተለጣፊነት የተፈለፈሉ ናቸው፡፡ ኢህአዴግ አምባገነን ባይሆን ሀገሪቱ ውስጥ ይህን ያህል ቁጥር ያለው ፓርቲ ባልተፈጠረ ነበር፡፡

ባለፈው ሳምንት ቅዳሜ አንድ ተስፋ ሰጪ ፖለቲካዊ እርምጃ ተስውሏዋል፤ ምርጫ ቦርድ የጠራው ስብሰባ አጋጣሚውን ፈጥሮላቸው የተቋውሞ ፊርማ በማሰባሰቡ ጉዟቸውን የጀመሩት 33ቱ ፓርቲዎች እነሆ ከምርጫ ባለፈ የጋራ ትግል ለማድረግ ፊርማቸውን አኑረዋል፡፡ ዲፕሎማቶች ታዋቂ ፖለቲከኞችና ጥሪ የተደረገላቸው ሌሎች እንግዶች በተገኙበት በተደረገው የፊርማ ስነ-ስርዓት የየፓርቲዎቹ መሪዎች በግልፅ እንደተናገሩት አምባገነን ስርዓት ለመታገል በጋራ ከመሰባሰብ የተሻለ አማራጭ የለም፡፡

ኢህአዴግም የፓርቲዎቹ ከምርጫ ውጪ በሆኑ ጉዳዮችም በጋራ ለመስራት መንቀሳቀሳቸው ስጋት ሳይፈጥርበት አልቀረም፡፡ ለዚህ ሁነኛ ማሳያ የሆነው ፓርቲዎቹ ለፊርማ ስርዓቱ ማስፈፀሚያ 11 አዳራሾችን ጠይቀው አስራ አንዱም ጋር እንዳይሰበሰቡ የተለመደው የኢህአዴግ ክልከላ መፈፀሙ ነው፡፡ የኢህአዴግ ተለጣፊ ፓርቲዎች፣ ፎረሞችና ሊጎች እንዳሻቸው የሚጠቀሙባቸው የህዝብ ንብረት የሆኑ የመሰብሰቢያ አዳራሾችን 33ቱ ፓርቲዎች እንዳይጠቀሙ መከልከሉ የኢህአዴግን ስጋት ከማረጋገጥ ባለፈ የስርዓቱ የጭቆና ልክ ገደብ እንዳጣም አመላካች ነው፡፡ ሌላው የገዢውን ፓርቲ ስጋት ማሳያ ኢህአዴግ ጥቂት የማይባሉትን የስብስቡ አባል የሆኑ ፓርቲዎችን በመከፋፈል መሞከሩ ነው፡፡ ከአዳማው የተቃውሞ ፊርማ በኋላ ስብስብ እንዲወጡና በምርጫ እንዲሳተፉ ጫና የተደረገባቸው ፓርቲዎች የምርጫ ቦርድን ፉከራና የኢህአዴግን ማስፈራሪያ ተቋቁመው ከምርጫ ባለፈ አብረው ለመስራት የስምምነት ፊርማቸውን ማኖራቸው ትልቅ ተስፋ ነው፡፡

> ከእንግዲህ ግን አዳራሽ ሲከለከሉ ‹‹ተከለከልን›› ብለው ስሞታ ከማሰማት ባለፈ በየአደባባዩ ስብሰባዎችን በድፍረት ማድረግ፤ አባሎቻቸው ሲታሰሩ “ታጋዮቻችንን ፍቱ” በማለት በተከታታይ ተግባራዊ ሰላማዊ ትግል ለማድረግ ይገባቸዋል፡፡

በእስከ ዛሬቹ የፓርቲዎች ስብስቦች እንደተስተዋለው በጋራ ለመስራት የሚሰባሰቡት ተመሳሳይ ፕሮግራም ያላቸው ፓርቲዎች ብቻ ነበሩ ፡፡ ሆኖም የኢህአዴግን አምባገነናዊ አፈና ለማስወገድ ከፕሮግራም መመሳሰል ያለፈ መሰባሰብ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ረገድ አዲስ ጅምር ያሳየው መድረክ ነው፡፡ መድረክ በህብረብሔራዊ አደረጃጀትና በብሔር አደረጃጀት ውስጥ ባሉ ፓርቲዎች ነበር የተመሰረተው፡፡ መድረክ ያሳየው በጎ ጅምር ለ33ቱ ፓርቲዎች ስብስብ ያበረከተው አስተዋፅኦ እንዳለ ግልፅ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ፓርቲዎቹ በተለያየ የፕሮግራምና የአደረጃጀት የሚከተሉ መሆኑ ሳያግዳቸው እነዲሰባሰቡ ሊያደርግ የሚያስችሉ በርካታ መሰረታዊ ችግሮች አሉ፤ የትኞቹም ፓርቲዎች የብሔር እኩልነት እንዲኖር፣ የህግ የበላይነት እንዲከበር፣ የሃይማኖት ነፃነት እንዲከበር፣ ሀሳብን የመግለፅና የፕሬስ ነፃነት እንዲከበር፣ የመደራጀት ነፃነት እንዲከበር እንደሚታገሉ ሲናገሩ ይደመጣል፡፡በመሆኑም እነዚህን መሰረታዊ መብቶች ለማስከበር የሚደረገውን ትግል በጋራ እንዳይታገሉ የሚያግዳቸው አንድም ምክንያት መኖር የለበትም፡፡

ፓርቲዎቹ በአደረጃጀት እና በፕሮግራም ልዩነት ግድግዳ ተከልለው ያባከኗቸውን 21 ዓመታት በኢህአዴግ አምባገነናዊ ስርዓት ስር የሚማቅቀውን የኢትዮጵያ ህዝብ መከራ ከማባባስ እና የገኘውን መደብ አባላት በእብሪት ተወጥረው እንዲከርሙ ከማድረግ ያለፈ ውጤት አላመጣም፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላማዊ ትግልን መርጠው የሚንቀሳቀሱ ፓርቲች በርካታ ውስጣዊና ውጫዊ ፈተናዎ አሉባቸው፡፡ ውስጣዊ ፈተናቸው መካከል የገንዘብ እጥረትና ብቃት ያላቸው አባላት እጦት የጎላውን ስፍራ ይይዛል፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት ፓርቲዎቹ ከሚያደርጉት ጥረት ጎን ለጎን የገንዘብ አቅም ያላቸውና የተማሩ ዜጎች ወደ ትግሉ ጎራ መምጣት አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው፡፡ ሌላው የፓርቲዎች ፈተና ውጫዊ ሲሆን በዋነኝነት ከአምባገነኑ የኢህአዴግ መንግስት የሚመነጭ ነው፡፡ ይህን ፈተና ለማለፍ ፓርቲዎች በቁርጠኝነት ወደተግባራዊ ሰላማዊ ትግል መግባት ይኖርባቸዋል፡፡ ኢህአዴግ አዳራሽ በመከልከል፣ አባላትን በማሰር እና ህዝብን በማሸበር የሚጓዝበት ጎዳና ፓርቲዎች በህዝብ ፊት አቅመ ቢስነታቸው እንዲጎላ አደርጓል፡፡ ፓርቲዎቹም ይህን ለመገዳደር ይሄነው የሚባል ጥረት አድርገዋል ለማለት አይስደፍርም፡፡ ከእንግዲህ ግን አዳራሽ ሲከለከሉ ‹‹ተከለከልን›› ብለው ስሞታ ከማሰማት ባለፈ በየአደባባዩ ስብሰባዎችን በድፍረት ማድረግ፤ አባሎቻቸው ሲታሰሩ “ታጋዮቻችንን ፍቱ” በማለት በተከታታይ ተግባራዊ ሰላማዊ ትግል ለማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ከሙስሊም ኢትዮጵያውያን ሰላማዊ የትግል መንገድ ብዙ ሊማሩም ይገባል፡፡ ተግባራዊ ሰላማዊ ትግሉ በአዲስ አበባ ብቻ የተወሰነ እንዳይሆን በተለያዩ ክልሎች እንዲስፋ ማድረግም ይገባቸዋል፡፡ የፓርቲዎች ስብስብ ከቢሮ ከታጠረ ‹‹ትግል›› ወደ ተግባራዊ ሰላማዊ ትግል መግባት አለበት፡፡




አንድነት ፓርቲ ማተሚያ ማሽን በመግዛት የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣን ህትመት ለማስቀጠል የገቢ ማሰባሰቢያ መርሀግብር ጀምሯል

እርስዎም :-

. ኩፖን በመግዛት

. የቃልኪዳን ሰነድ በመሙላት

. አቢሲኒያ ባንክ ጠመንጃ ያዥ ቅርንጫፍ የባንክ ሒሳብ ቁጥር 47 ገቢ በማድረግ አጋርነትዎን ያረጋግጡ

ለተጨማሪ መረጃ

0933-89-17-66 እና

0933-89-17-67 ይደውሉ

udjparty@gmail.com

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ወደ ህትመት እንድትመለስ በመርዳት መረጃ የማግኘት መብትዎን ያስከብሩ!!

ፍኖተ ነፃነት

የኢትዮጵያን ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ